ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

# ምርጫ 2002 በተመለከተ የግንቦት 7 አቋም ማብራሪያ

ቀን ሐምሌ 23 2001

## 1. መግቢያ

ወያኔ ምርጫ 2002ን በተመለከተ የመራጩንና የተወዳዳሪውን ገደብ፤ የሚያመቸውን ጊዜና የምርጫ ዳኛውን በዚያውም የምርጫውን ውጤት ነድፎ ጨርሷል ... እኛስ?

እንደሚታቀው አብዛኛዎቹ የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አባላት በግንቦት 1997 ምርጫ ንቁ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ የንቅናቄውም ከፍተኛ አመራር እንዲሁም በ1997 ምርጫ በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፈ ነው፤ ስለምርጫው በቂ እውቀት አለው፡፡ አመራሩ የምርጫ 97 ልምድን አበጥረው መርምሯል፡፡ የግንቦት 7 ንቅናቄ ከዚህ ምርምር በመነሳት አሁን አገራችን በምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ ምርጫ የሚኖረውን ትርጉም በግልጽ አስቀምጧል፡፡ «ምርጫ የሕዝብን ድምፅ ህገወጥ በሆነ መንገድ ቀምቶ በጠመንጃ ኃይል ዘረኛና ዘራፊ አገዛዙን የዘረጋውን አምባገነናዊ የወያኔ አገዛዝ ህጋዊ እውቅና መስጠትና ማጠናከር ይሆናል» ብሏል፡፡ «በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት የሚቻለው የሥርዓቱን ግፈኛ ገጽታ ለመሸፈን ወያኔ በሚጠራው ምርጫ አይደለም፡፡ እንዲያውም በአገራችን እውነተኛ ምርጫ ማድረግ የሚቻለው ወያኔ ከሥልጣን ተወግዶ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ባቀፈ የዲሞክራሲ የሽግግር ሂደት ማለፍ ስትችል ብቻ መሆኑን» ግንቦት ሰባት በማያሻማ ቋንቋ ገልጧል፡፡ ግንቦት 7 ይህንን አይነቱን የሽግግር ሂደት በአገራችን ለማስጀመር ዲሞክራሲያዊ ራዕይ አንግቦ፣ ማኛቸውንም የትግል ስልት በመጠቀም ከሕዝብና ለዴሞክራሲያ ሂደቱ መጀመር ቅድሚያ ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር በመደጋገፍ መራራውን ትግል ጀምሯል፡፡ ያም ሆኖ የ2002 የወያኔ የምርጫ ቲያትር ጊዜ እየደረሰ ነው፡፡ ይህን ተንተርሶ የተጠበቁና የማይቀሩ የማደናገሪያ እርምጃዎቹን ወያኔ መውሰድ ጀምሯል፡፡ ሕዝቡና የተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ እንዲሁም በሃገራችን ያሉት የዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ አባላት ለዚህ የወያኔ እስክስታ የሚመልሱት መልስ ሕዝባዊ ውይይት ስለሚያስፈልገው የንቅናቄያችንን አቋም ለመግለጽ ይህንን ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

## 2. ምን ዓይነት ምርጫ፡ ነፃ ወይስ የሴራ ምርጫ?

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማለቅ በኋላ በታዳጊው ዓለም ጎራ ያሉ ሁሉም ዓይነት መንግሥታት ምርጫን የሥልጣናቸው ሕጋዊና ሞራላዊ መሠረት ለማድረግ እየሞከሩ ነው። ይህ የምርጫ ሙከራ እንደተጀመረም በምርጫ ወደ ሥልጣን የወጡትን መንግሥታት ከዚህ በፊት ከነበሩት ፈላጭ ቆራጭ የነገሥታት፣ የወታደራዊና የአንድ ፓርቲ አገዛዞች ጋር በማነጻጸር የተሻሉ ጅምሮች ናቸው የሚሉ እምነቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረው ነበር። ምናልባትም እነዚህ ምርጫዎች በሂደት ወደ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመሄጃ በር ይከፍቱ ይሆናል በሚል መላምት በደፈናው እንደ መሻሻል የታዩበት ሁኔታ ተከስቶ ነበር። ከ 20 ዓመታት ልምድ በኋላ የታየው ተጨባጭ ሁኔታ ግን ቀደም ተብሎ ተይዞ የነበረውን ተስፋ ያደበዘዘ ሆኗል፡፡ እርግጥ ነው ጥቂት ምርጫዎች እውነተኛ የሆነ የዴሞክራሲ ሂደትና ግንባታ በጥቂት ሃገሮች ላይ እንዲጀመር አስችለዋል፡፡ ብዙዎቹ ምርጫዎች ግን ከቀድሞው ባልተሻለ ሁኔታ የፖለቲካ ጭቆና፣ የኢኮኖሚ ገፈፋና የጥቂት አምባገነኖች ግፈኛ አገዛዝ የመከለያ ሽፋን ሆነው አርፈውታል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዓለማችን ውስጥ አራትና አምስት አመት እየጠበቁና አስመሳይ ምርጫቸውን እያካሄዱ የአንድ ፓርቲ ወይም የአንድ ግለሰብ አገዛዛቸውን በምርጫ ስም የህጋዊነትና የሞራል ልባስ ለማለበስ ሙከራ የሚያደርጉ አምባገኖች ቁጥራቸው እየተበራከተ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች በሥራ ላይ እየዋለ ያለው በማጭበርበር ሴራ ላይ የተመሰረተ ምርጫ ውጤቱ በጥቂቶች የበላይነት በዘር የተደራጀ የፖለቲካ ሥርዓት ማጠናከር ሆኗል፡፡ ከአገሪቱ ሕዝብ 5 በመቶ የማይበልጠውን የትግራይ ህዝብ «በትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭነቱ እወክላለሁ» የሚል ነገር ግን የእዚህ ውክልና እንዳለው ግን ምንም አይነት ዴሞክራሲያዊ ማረጋገጫ የሌለው ጠባብ ቡድን፣ ዘረኛ አገዛዙን በመላው አገሪቱ ህዝብ ላይ የሚጭንበት የማጭበርበሪያ ስልት ምርጫ ሆኗል፡፡

ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው ሁለት ዓይነት የምርጫ ልምዶች በመነሳት በአሁኑ ጊዜ የዲሞክራሲና የምርጫ ሂደት የሚከታተሉና የሚመረምሩ ጋዜጠኞችና ተመራማሪዎች ምርጫን በሁለት ቦታ ከፍለው እንዲያዩ ተገደዋል።

በአንድ በኩል ምርጫ የፖለቲካ ቡድኖች ትርጉም ባለው መልክ ተወዳድረው የሕዝብ ውክልና እና ተጠያቂነት ያለው መንግሥት መመሥረቻ ሁኗል። በዚህም ሂደት አገራት ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን እየገነቡና እያጠናከሩ፣ በማኅበረሰባቸው ውስጥ ዲሞክራሲ ባህልና አሰራር እንዲጎለብት፣ ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ እሴቶች ከፍተኛ ክብር እንዲሰጥ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ከእነዚህም አገሮች ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ እድገት መሰላል፤ የሰላምና የመረጋገት ዋስትና፤ የማኅበራዊ ችግሮች ማቃለያ እና የሰብአዊ ክብርና መብት ማስጠበቂያ መሣሪያ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ አምባገነኖች ምርጫን የሚፈልጉት ሥልጣናቸውን ሞራላዊና ህጋዊ ለማድረግ ብቻ እንደሆነ ግልጽ ሆኗል፡፡ እነዚህ አምባገነኖች በአንድ በኩል የመንግስት ሥልጣን መያዝ ያለበት በሕዝብ ነጻ ፈቃድ ላይ በተመሠረተ ምርጫ ነው የሚለው እሳቤ የሆነው የዘመኑ የሰው ልጆች ሁሉ ገዢ እምነት መሆኑን ተረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ገንዘቡና ጉልበቱ ያላቸው በርካታ የዓለም አገሮች ለዴሞክራሲና ለምርጫ ትልቅ ቦታ እየሰጡ መምጣቸው ገብቷቸዋል፡፡ ይህ እውነታ አምባገነኖች እንደቀድሞው «የምን ምርጫ! የምን ዴሞክራሲ!» ብለው እየደነፉ መቀጠል የማይችሉበትን ሁኔታ እንደፈጠረ ያውቃሉ፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ድሃና የመንግሥታዊ በጀታቸው ከፍተኛ መጠን ያለው ድርሻ በምዕራብ መንግሥታት እርጥባን የሚሟሉላቸው፤ የራሳቸው ኢኮኖሚያዊ ሉዓላዊነት የሌላቸው አገራት ገዥዎች እንደ ቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ለብድርና ለእርዳታ የሚሄዱበት ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ሳይወዱ በግድ የዴሞክራሲ ጨዋታ ውስጥ እንዲገቡ ተገደዋል፡፡ የዓለማችን የደሃ አገራት አምባገነን መሪዎች የዴሞክራሲና የምርጫ ጨዋታ ውስጥ ሳይገቡ ከምዕራባውያን የሚያገኙት እርዳታ ቀጥ ሊል እንደሚችል ስለሚውቁ ስለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሃሰት መዝሙራቸውን ለመዘመር ተገደዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ቢያደርጉ አምባገነናዊና በሙስና የተበከለ የገዥነት ታሪካቸው በቀላሉ በምርጫ ተሸንፈው ከሥልጣን እንዲነቀሉ የሚያደርጋቸው መሆኑን ይረዳሉ፡፡ ከእዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ውጤቱን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት፤ እነሱን ከሥልጣን መንቀል ቀርቶ ሥልጣናቸውን ሊገድብ እንኳን በማይችል መንገድ ውጤቱ አስቀድሞ የታወቀ የይስሙላ ምርጫ ማድረግ ከሁሉ የተሻላ አማራጭ አካሄድ ሆኖ አግኝታል፤ ዝርዝር አሠራሩንም ሰልጥነውበታል፡፡ እንዲህ አይነቱ የማስመሰልና የማጭበርበሪያ ምርጫ የሚያደርጉ የዓለማችን አምባገነን ኃይሎች በርካታ መሆናቸው ፀሐይ የሞቀው ሚስጢር እየሆነ መጥቷል። ይህም ግንዛቤ የዓለማችንን የዲሞክራሲ ሂደት በአትኩሮት ከሚመለከቱት ታዛቢዎች አልፎ በአምባገነኖች ሥር ያሉ ሕዝቦች ሁሉ የተረዱት ሃቅ ሆኗል፡፡ ይህ እውነታ ደግሞ አምባገነኖች ምርጫን እንዳሻቸው መቆጣጠር የሚችሉበት አቅማቸውና ብልጣብልጥነታቸው በሙሉ ተሟጦ ማለቅ መጀመሩን ያሳያል።

በይስሙላ ምርጫ የአገሩን ሕዝብና ዓለም-ዓቀፍ ማኅበረሰብን ማጭበርበር እንደማይችሉ የተረዱ አንዳንድ አምባገነኖች የማፈግፈግ እርምጃን ሲመርጡ (ለምሳሌ ኬንያና ዚምባብዌ) ሌሎቹ ግን ባገጠጠ መልኩ ሕዝብን የማፈንና የማስፈራራት እርምጃዎችንና ምርጫንም ከበፊቱ በባሰ በማጥበብ መሄድን መርጠዋል። (ለዚህ አይነቱ እብሪት የመለስ-በረከት አገዛዝ ሁነኛ ምሳሌ ሲሆን ግብፅና ምናልባትም ኢራን በሰሞኑ አካሄዳቸው ከቀጠሉ ተከታይ ምሳሌች ሊባሉ ይችላሉ)።

ወያኔ ምርጫን ምን ያህል በሙሉ ቁጥጥሩ ውስጥ እንዳስገባውና በማስመሰያነት እንደሚጠቀምበት ለመገንዘብ በ2000 ዓ.ም የአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫዎች የተጫወተውን ቲያትር መመርመር በቂ ነው። በአዲስ አበባ ውስጥ ከሁለት ዓመታት በፊት አንድ ተመራጭ ማስመረጥ ያቃተው ወያኔ በዚህ ምርጫ «የከተማው አቸናፊ ተመራጮች ሙሉ በሙሉ የእኔ እጩዎች ናቸው» አለ። ይህ በተዓምር ደረጃ ሊታይ የሚገባው ጉድ የሚያመለክተው የመለስ-በረከት ቡድን የሕዝብን ልብ የመቀየር ቀዶ ጥገና እውቅቱ እጅግ የረቀቀ፣ በዓለማችን ተሰምቶና ታይቶ ከማይታወቅ ደረጃ መድረሱን ነው። በተባባሰ ግድያ፣ እስራት፣ አፈናና ዘረፋ የሶስት አመት ግዜ፣ ወያኔ በአዲስ አባባ ውስጥ ከዜሮ ወንበር ወደ ሁሉንም ወንበር ባለቤትነት የተሸጋገረበት ሁኔታ የሚያረጋግጠው ያለ ዕውነተኛ የውድድር ቅድመ ሁኔታዎች ምርጫ ምንም ፋይዳ እንደሌለው ነው፡፡

### 2.1. የነፃ ምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች ምን ይመስላሉ?

ከላይ እንደጠቀስነው ከ20 ዓመታት የምርጫ ማጭበረበር ልምዶች በኋላ አምባገነኖች ለክተው በሰጡን መጠን ወንበር ተቀብለን ይህን ድርጊታችንን የዲሞክራሲ ሂደት ነው ብለን እርስ በርሳችን መከራከር የማንችልበት ህዝባችንንም ማጭበርበር ከማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በተለይ በ97 ምርጫ የድል ተራራ አፋፍ ላይ ደርሶ በወያኔ አጋዚ ጦር አሽቆልቁሎ እንዲመለስ የተደረገን የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ወያኔ ሥልጣኑን ቅንጣት እንኳን በማትነካው መልኩ በሰጠን ወንበር ውስጥ ለመቀመጥ ብቻ ወያኔን በምርጫ ተብዬ ቀልድ ማጀብ የሕዝብ ወገኖች ለሆኑ ሁሉ በጭራሽ የማይመጥናቸው ተግባር ነው ብለን እናምናለን።

የሕዝብን ስሜት የሚያስተጋቡ ተቃዋሚዎች ከአሁኑ ፈጥነው ማድረግ ያለባቸው ምርጫ ለአምባገነኖች የህጋዊነትነትና የሞራል ሽፋን መስጫ ሳይሆን እውነተኛ የሕዝብ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት፣ ይህ ፍላጎት ብቻ የአገርን፣ የመንግሥትንና የዜጎችን እጣ የሚወሰን ልዕልና ያለው የሚሆንበትን ሁኔታ እንዴት እንፈጠራለን ለሚለው ጥያቄ አንስተው መልስ መስጠት ነው፡፡ ባጭሩ እነመለስ በተጭበረበረ ምርጫ ዘረኛ፣ አምባገነናዊና የዘረፋ ስርአታቸውን የማስቀጠል ሥራ እየሰሩ መሆኑን በመረዳት መጪው ምርጫ በተጻራረው የሕዝብ ፍላጎት በነጻ የተገለጸበት ምርጫ እንዲሆን ለማድርግ አቅዶ መንቀሳቀስ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የቅንጅት መሪዎች እንዳደረጉት ድምጹን የተዘረፈውም ህዝብ ድጋፉን በደሙ ሳይቀር እንደሰጠበት፣ ምርጫ የአምባገነንነት መጋረጃ ሳይሆን በእውነት ለመንግሥት ሥልጣን መወዳደሪያ እንዲሆን የሚያስፈልጉትን አገራዊ ቅድመ ሁኔታዎች ዘርዝሮ፣ ለእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች የኢትዮጵያን ሕዝብና የወያኔ አፈና አላነቃንቅ ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ በማስተባበር መታገል ነው፡፡ ይህን

ትግል በውጭ በሚገኘውና ትልቅ አስዋጽኦ ማደረግ ወደሚችለው ኢትዮጵያዊም ማድረስ ይገባል፡፡ ሃቀኛ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖር መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በአገርችንና በአካባቢያችን ጉዳይ ያገባናል ለሚሉ፣ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ብሄራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችን ይነካል ብለው ለሚያስቡ የዲፕሎማሲያዊ ማኅበረሰባትና ለራሱም ለወያኔ ማቅረብ ያስፈልጋል። በዚህ በኩል እስካሁን መኢአድ ያደረገው በአርአያነቱ የሚጠቀስ ነው።

## 2.2. ለመሆኑ ዓለም የሚያውቃቸው የእውነተኛ ውድድር ምርጫ መለያዎች ምንድር ናቸው?

ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት የግድ ነፃ (free) እኩልና (fair) ታማኝነት ያለው (credible) የፖለቲካ ሜዳ ተፈጥሮ፣ የፖለቲካ ቡድኖች የሚወዳደሩበት መድረክ ነው። ለዚህም፡-

- አስመራጩ (የምርጫ አስፈፃሚው) አካል ከአንድ ፓርቲ ቁጥጥርና ተጽእኖ ነጻ ሆኖ የተደራጀ፣ በነፃ አሠራርና በገለልተኛነት ሥነ ምግባር የዳበረ ቡድን መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ሥልጣን በግልጽ በተደነገጉ በሥልጣን መባለግ እንዳይኖር በሚያደርጉ ሕጎች የተከፋፈለና ተጠያቂነት ያለበት፤ ይህም በተግባር የተመሠከረለት መሆን አለበት፡፡
- የአገሪቱ የፍትህ ሥርዓት በቅልጥፍና፤ በእኩልነትና ከሕግ አስፈጻሚው ነፃ በሆነ መልኩ ሲሠራ የታዬ መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ወታደር፤ ፖሊስ፤ የፀጥታና እንዲሁም ሲቪል አስተዳደሩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥጥር ውጭ መሆን አለበት፡፡
- የመንግሥት ሀብት ተቀናቃኝ ፓርቲዎችን ማዳከሚያ፣ በምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት መጠቀሚያ፣ ዜጎች የገዥው ፓርቲ አባላት እንዲሆኑ የመግዣና የማስገደጃ መሣሪያ መሆን የለበትም፡፡
- የመንግሥት ሚዲያም ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ለሁሉም ዜጎች መገልገያ በሚሆንበት መልኩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ መደራጀት ይኖርበታል፡፡

እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት አገር እንኳን እንደ ወያኔ ባለ ለአስራ ስምንት ዓመታት በማጭበርበር የታወቀ ገዥ ቡድን ቀርቶ በሌሎችም ለዘብተኛ አገዛዞች በሚገኙባቸው አገሮች እንኳን ሃቀኛ ውድድር ያለበት ምርጫ ማድርግ እንደማይቻል ተደጋግሞ ታይቷል። ከእዚህ ተነሰተን እስኪ ወያኔ በምርጫ ግጠሙኝ እያለ በተቃዋሚዎች ላይ የሚፏልልበት የአገራችንን ወቅታዊ የምርጫ ሁኔታ ምን እንደሚመስል እንመልከት፤

- አገራችን በመለስ ፈቃድ ብቻ የሚንቀሳቀስ የምርጫ ቦርድና መለስ እንዳሻው የሚሾማቸውና የሚሽራቸው የምርጫ ቦርድ አባላት አሏት፡፡ ከእነዚህም መሃል አብዛኛዎቹ የወያኔ ካድሬዎች ናቸው፡፡
- አገራችን በወያኔ በጎ ፈቃድ ብቻ የሚዘወር የወያኔ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ የሆነ የፌደራልና የክልል መንግስታት መገናኛ ብዙሃን ያለባት አገር ናት፡፡ የግል የተባሉ ጥቂት ራድዮ ጣቢያዎች በሙሉ በወያኔ ካድሬዎችና በወያኔ ካፒታልና ፈቃድ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ የግል ጋዜጦችም በወያኔ አፋኝ የፕሬስ ህግና የአፈና ተቋማት በነጻነት እንዳይዘግቡ የቀፈደዱ ናቸው፡፡
- አገራችን መለስ ዜናዊ በአንድ ቀን ውስጥ የፈለገውን (የገዛ ህገ-መንግሥቱን ጭምር የሚጥስ) ህግ ለማውጣት የሚያስችለው በመለስ የሚታዘዝ ፓርላማ ያለባት አገር ናት፡፡ መለስ ዜናዊ ለዳኞች ስልክ ደውሎ፣ የብይን ውሳኔያቸው ምን መሆን እንደሚገባው ትእዛዝ የሚሰጥባት ሃገር ናት፡፡ ዳኞች፣ አቃቤ ህጎችና መረጃ አቅራቢ ፖሊሶች በሙሉ የወያኔ ካድሬዎች ናቸው፡፡
- አገራችን፣ መለስ የምርጫ ውጤት ካልተስማማው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያውጅባት፣ በመለስ ትእዛዝ ሰላማዊ ስልፈኞችን እያነጣጠረ ግንባርና ልብ ላይ የሚተኩስ ነብሰ ገዳይ፣ ልዩ ጦር መኖሩ በግልጽ የታየባት አገር ናት፡፡
- <u>ከሁሉም በላይ</u> ሃገራችን በግምት ሳይሆን በተግባር በምርጫ 97 እንደታየው፤ ነፃ ምርጫ ከተደረገ የወያኔ መንግሥት ከስልጣን ሊወገድ የሚችልባት አገር ናት።

ከላይ የጠቀስናቸው ነጥቦች በአገራችን ነጻና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ፣ ፕሬስ፣ የፍትህ ሥርዓት፣ የፖሊስ፣ የሰለላና የመከላከያ ኃይል አለመኖራቸውን የሚረጋግጥ ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት የሉም ማለት ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ሊኖር አይችልም ማለት ነው፡፡ ይህ ድምዳሜ በሂሳብ 1 ሲደምር 1 ሁለት ይሆናል ከሚለው ሎጂክ ምንም ልዩነት የሌለው ነው፡፡ በምንም ምክንያት የሚለወጥና የሚቀየር አይደለም፡፡ የመጨረሻው ነጥብ ደግሞ የሚያሳየን፤ እውነተኛ የሕዝብ ወገን የሆኑ ሁሉ በኢትዮጵያ ስለምርጫ ሲያስቡ የማሸነፍ እድላቸው በተግባር የታየና የሚቻል መሆኑን እራሳቸውም አምነው ለሕዝቡም ይህንን ሁኔታ በመግለጽ መሳተፍ የሚገባቸው መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ የማሸነፍ እድላቸው ዛሬ ጠቦ የሚታየው ወያኔ ከግንቦቱ 1997 ምርጫ በኋላ የወሰዳቸው የእመቃ እርምጃዎች ውጤት እንጂ ድርጅቶቹ ከወያኔ በማነሳቸው ህዝቡም ያኔ ላይ የነበረው ምሬት በድንገት ወደ ፍቅር በመቀየሩ እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ከእዚህ ተነስተው ለማናሸንፍበት ምርጫ ለምን እንገባለን የሚል አቋም ከመውሰዳቸው ወይም ለማናሸንፍበት ምርጫ ወያኔን የወሰነልን ወንበር ተቀብልን መሰንበት የሚል ውሳኔ ላይ ከመድረሳቸው በፊት በነጻና በፍትሃዊ ምርጫ ወያኔን ከሥልጣን ማባረር እንደሚችሉ በራሳቸው መተማመን ይኖርባቸዋል፡፡ ምርጫ 97 ያስተማረን ቁም ነገር ቢኖር በተቃዋሚዎች ላይ ትልቅ ንቀት የነበረው ወያኔ በራሱ ተማምኖ በከፈታት የዴሞክራሲ ቀዳዳ ተቃዋሚዎች ወያኔን በቀላሉ

ከሥልጣን ሊያባርሩት እንደሚችሉ ነው፡፡ ችግሩ ያለው የዴሞክራሲ ምህዳሩ መጥበብ ላይ እንጂ ህዝብ በወያኔ ላይ መማረሩን ስላቆመ እንዳልሆነ መተማመን ያስፈልጋል፡፡ ሕዝብ የነጻ ምርጫ እድል ቢሰጠው አሁንም ከ1997ቱ በከፋ መልኩ ወያኔን የሚተፋው መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ምህዳሩ ቢሰፋ የነጻና የፍትሃዊ ምርጫ ሂደት ቢጀመር ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአጭር ግዜ ውስጥ ተሰባስበው በጋራ ወያኔን ገጥመው ሊያሸንፉት የሚችሉበትን መርሃ ግብር መዘርጋት፣ የሕዝብንም ድጋፍ ማግኘት እንደሚችሉ በራሳቸው ላይ መተማመን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ በተግባር በ1997ቱ ምርጫ የታየ ስለሆነ ተቃዋሚዎች ወያኔ የሚነዛውን የቅስም ሰበራ ፕሮፓጋንዳና ጭቆና ራሳቸውም ሆኑ ሕዝብ መቋቋም እንዲችል በጋራ መታገል ይኖርባቸዋል። በተጻራሪው መንግሥት አሁን ካለው የመጨቆን አቅም ተነስተው ግን ማሸነፍ እንደማይቻል ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው። ከዚህ የተሸናፊነት መንፈስም በመነሳት የመለስ-በረከት ቡድን አስልቶ የፈቀደልንን ወንበር መያዝ መሻሻል ነው ብለው ካሰቡ ደግሞ የከፋ ስህተት ይፈጽማሉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ውሳኔ የሀገሪቱን ሁኔታና የሕዝብን ፍላጎትና ችሎታ አለመረዳት ይሆናል። ሰሙ-ጥሩ የተቃዋሚ ሰዎች ወያኔን አጅበው ለወያኔ አሸናፊነት በተመቻቸ ምርጫ ከገቡ የዚህ ተግባር ዋና ውጤቱ በሀገራችን ውስጥ በዘር መድሎና በአምባገነንነት ላይ የተዘረጋውን ሥርዓት እድሜ ማራዘም ይሆናል።

## 3. ወያኔና የ2002 ምርጫ

የ2002ቱ ምርጫ ገና አንድ ድምፅ ከመሰጠቱ በፊት ወያኔ አሸናፊነቱን የተረጋገጠ ለማድረግ በሁለት ምዕራፎች የተከፋፈለ መርሃ ግብር ነድፎ መንቃነቅ ከጀመረ ሰንበቷል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የተቃዋሚ ኃይሎችንና የሲቪል ማኅበራትን ማዳከም እና የሕዝብን ቅስም መስበር ሲሆን፤ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ እራሱ መጥኖ በሚከፍታት ጊዜና ሁኔታ የአስመሳይ ምርጫ "ውድድርን" ማኪያሄድ ነው።

ተቃዋሚዎችን በማዳከም ዙሪያ ወያኔ እስካሁን ያደረጋቸው ዋና ዋና እርምጃዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

- ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ደግፈዋል፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በአመራርነትና በአባልነት አገልግለዋል ባላቸው ላይ የግድያ፣ የእሥራትና የማሳደድ ውርጅብኝ አውርዷል፡፡ ወያኔን ክፍኛ ያስደነገጠውን ትልቁን የፖለቲካ ድርጅት ቅንጅትን አፍርሶ, የመሪዎችን የፖለቲካ ነጻነት ሸምግልና በሚል ሸፍጥ ገድቦ፤ እንኳን ለነጻና ፍትሃዊ ምርጫ መካሄድ አስፈላጊ የሆኑትን የተቋማት ጥያቄዎች ማነሳት ቀርቶ እነሆ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን ውሸትን እውነት ካላልሽ ብሎ ወህኒ ወርውሯት እያየን ነው፡፡
- የአገዛዙ የፀጥታ ኃይል የተቃዋሚ ድርጅቶች በየጽሕፈት ቤታቸውና በየክልሉ ያሰማሯቸውን ሠራተኞችና አስተባባሪዎች በገንዘብ በመደለል፤ በማስፈራራትና ከዚያም አልፎ በማሠር ድርጅቶችን ያለ አደራጆች ለማስቀረት በየቀኑ ወንጀል እየፈጸመ ነው።
- ለተቃዋሚዎች ቤትን የሚያከራይ ማስጠንቀቂያና እንግልት ሲደርስበት፤ ይህንንም እየፈራ ቤቱንና የመሰብሰቢያ ቦታዎችን ለተቃዋሚዎች አናከራይም የሚለው ባለ ሀብት ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው።
- ተቃዋሚዎች በየጊዜው ለሚጠይቁት ሕዝብን በአደባባይ የመሰብሰብ ጥያቄ በየምክንያቱ «አይቻልም» የሚል ምላሽ መስጠት የተለመደ ነው። በዚህ ተደጋጋሚ ክልከላ ሳይሰላቹ በጥያቄ ብዛት ስብሰባ በተወሰነ ቦታ የሚፈቀድላቸው ተቃዋሚዎች ደግሞ የተሰበሰበውን ሕዝብ ለማሸማቀቅና ከዚህ በፊት እንደታየውም ለስለላ ሥራ ለማዋል የመንግሥት "ጋዜጠኞች" ስብሰባውን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው፣ በእንያዳንዱ ተሰብሳቢ ፊት ላይ እያነጣጠሩ በቪዲዮ ይቀርጻሉ። *(እነዚህ "ጋዜጠኛ" ተብየዎች የቀዱትን ስብሰባ ለአንዷት ሰከንድ እንኳ በመገናኛ ብዙሃን ሲያሰሙት አይታይም።)*
- የታወቁ የተቃዋሚ ድርጅቶችን የከፍተኛ አመራር ስብሰባ ሂደቶችን የመንግሥት የስለላ ቡድኖች በተደበቁ ኤሌክትሮኒክስ መቅጃዎች በመቅረፅ፣ በስለላ ክፍሉ በነፃ ጋዜጣ ስም በተቋቋሙ ጋዜጦች ለሕዝብ በማቅረብ በተቃዋሚ መሪዎች መካከል አለመተማመንን ለመፍጠርና ከዛም አልፎ የተቃዋሚ መሪዎችን በሕዝብ ፊት ደካማ አድርጎ ለማሳየት አገዛዙ ሥራዬ ብሎ ተያይዞታል።[1]

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ባላነሰ ሁኔታ ለዲሞክራቲክ የፖለቲካ ሕይወት እስትንፋስ የሆኑትን የሲቪኽ ማህበራትንና የነፃ ፕሬስን ለማዳካም ከወሰዳቸው እርምጃዎች በትንሹ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤

- የስቪክ ማኅበራትን ነፃና ገለለተኛ አሠራር ጨርሶ የሚያጠፉ ሕግ እንደ ሎሌው በሚያዘው ፓርላማ አማካኝነት ደንግጓል።[2] በተመሳሰይ ሁኔታም ወያኔ የነፃ ፕሬሱ ሕዝቡን የሚያገለግልበትን መንገድ በሕግ አጥሯል፡፡

---

[1] *በነገራችን ላይ ይህ የወያኔ ተግባር በዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ምን ያህል ወንጀል እንደሆነ ለማወቅ በአሜሪካን ሀገር ውስጥ በ 1970ዎቹ የዋተርጌቱ ቅሌት ተብሎ ፕሬዝዳንት ኒክሰንን ከሥልጣን እንዲወርዱ ያደረገውን ታሪክ ማስታወስ ይበቃል። የዋተርጌቱ ቅሌት በምርጫ ወቅት የፕሬዝዳንቱ ፓርቲ በሆነው የሪፐብሊካን ፓርቲ አባላት አማካኝነት በተወዳዳሪው የዲሞክራቲክ ፓርቲ ጽ/ቤት ሰብሮ ለመግባት ሙከራ ሲያደርግ የተያዘበት ነው። በዚህ ምክንያት ፕሬዝዳንቱ ከሥልጣን ሲባረሩ ብዙ ሰዎች ደግም ለረጅም ዓመታት ለእስር ቤት ተዳርገዋል። ወያኔ ግን ይህንን መሰል ሥራ ተቃዋሚዎች ላይ ደጋግሞ ሲፈጽምና በግልጽ ለሚታወቁ የራሱ የሆኑና ደጋፊዎቹ የሚዲያ ምርቶች እየሰጠ ሲደነፋ ወንጀል መሥራቱን እንኳን አያውቀውም።*

[2] *እዚህ ላይ አንድ የሚያስቅም፣ የሚገርም ታሪክ አለ። ይህ የሲቪክ ማሕበራትን የሚያፍነው ሕግ አንድ አንቀጽ ማሕበራቱ ከ 10% በላይ የሚሆን የገንዘብ እርዳታ ከውጭ ካገኙ ማሕበራቱ እንደ የውጭ ሀገር ማሕበር ተመዝግበው ሥራቸውን ሁሉ ለመንግሥት የስለላ ኃይሎች ሙሉ በሙሉ ክፍት እንዲያደርጉ ይጠይቃል። እዚህ ላይ የሚአስቅም የሚገርምም ጉዳይ ያልንበት ምክንያት የወያኔ መንግሥት እራሱ ከ30% በላይ የመንግሥት ባጀቱን የሚያገኘው ከነዚህ የሲቪክ ማሕበራቱን ከሚረዱ መንግሥታት መሆኑ ነው። የዚህን የወያኔን የሕግ ረቂቅ አስተሳሰብ (ሎጂክ) በራሱ መንግሥት ላይ ብንጠቀምበት ወያኔ በገዛ ሕጉ የውጭ ሀገር መንግሥት ይሆናል ማለት ነው።*

- በቅርቡ ደግሞ ይባስ ብሎ ሕዝቡን የማሰብ ነፃቱን እንኳን የሚጻረር “ጸረ-ሽብርተኛ” የተሰኘ ሕግ በአዛው የመለስ መሃተም ሆኖ በሚገለግለው ፓርላማ አጸድቋል።
- ይህም ሳይበቃው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይነተኛ ወያኔን መቃወሚያ የሆነውን ሰንደቃላማውን ማውለብለብ እንኳን ሕገ-ወጥ የሚያደርግ ሕግ በአሁኑ ሰዓት እያረቀቀ ነው።

በመጨረሻም ሕዝብ በምርጫ ለውጥ ይቻላል የሚለውን እምነት ጨርሶ ከአዕምሮው አውጥቶ በምትኩ የሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ከወያኔ በጎ ፈቃድ ጋር እንደተያያዘ ቆጥሮ በፍርሃት እንዲወጥ የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካና የስነልቦና ጦርነት ያለማቋረጥ ተደርጎበታል፡፡ ለማስረጃም ያህል

- የምርጫ 97 ዋና ዋና ተሳታፊ የነበሩ ወጣቶችን፤ ነጋዴዎችና የገጠር ነዋሪዎችን በእሥር፤ በስደትና በሞት ሲቀጣ ሌሎችን ደግሞ እየተጠሩ በማስፈራራት፤ በመተዳደሪያ ሥራቸውና ንግዳቸው ላይ እገዳ በማድረግ፤ ሥራን በማሳጣት፤ ያለአግባብ ግብር በመጫን … ሁለተኛ ከተቃዋሚ ጎን እንዳይቆሙ ያስፈራራል።
- ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ሥራ ፍለጋ የሚሰማራውን ተመራቂ ወጣት ሥራ ለማግኘት ወያኔን መደገፍና የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች ውስጥ አባል መሆን ግዴታ እያደረገበት ነው።
- በማንኛወም መንገድ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ግንኙንት የሚፈጥር ሰው በራሱና በቤተሰቦቹ ኑሮና ደህንነት ላይ አደጋ እንደሚፈጠር ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ይነገረዋል።

ከላይ በተዘረዘሩት እርምጃዎች አማካይነት በምርጫ 2002 አሸናፊ አድርጎ የሚያወጣውን «ተቃዋሚዎችን የማዳከም፤ የሲቪል ማኅበራትን የፖለቲካ ተሳትፎ ማጥበብንና የሕዝብንም ቅስም የመስበር የምዕራፍ አንድ ዝግጅቱን አጠናቅቂያለሁ ብሎ» አምኗል። የሁለተኛው ምዕራፍ መርሃ ግብሩን ደግሞ በቅርቡ እንደሚጀምር አንዳንድ ሁኔታዎች እያመለከቱ ነው። በዚህ በሁለተኛ ምእራፍ የሚጠበቀው ዋነኛ እርምጃም ወያኔ ለራሱ በተመቻቸ የጊዜ መስኮት ውስጥ ለምርጫ ውድድር ዝግጁ ነኝ ብሎ ማወጅና ለምርጫውም አጃቢዎችን መፈለግ ነው። ለዚህም የሚጠቀምበት ዘዴዎች የሚከተሉትን እንደሚመስሉ ይጠበቃል፤

- በአለቀ ሰዓት ለሚሳተፉ ተቃዋሚዎች የተወሰነች የሚዲያ ዕድል መስጠት፡ ይህም እድል እንደ ምርጫ 97ቱ ለፓርቲዎች የሚሰጥ ሳይሆን ለግለሰብ ተወዳዳሪዎች እንዲሆን ማድረግ፤ በዚህም ከ500 በላይ የፌደራል ፓርላማ ተወዳዳሪና በሺዎች የሚቆጠር የክልል ተወዳዳሪ በሚሰጠው 5 ደቂቃ ምንም ሳይናገር ጊዜውን እንዲጨርስ ማድረግ፤
- ከተወሰነላቸው ወንበር በላይ ለማሸነፍ ዕድሉም ሆነ የመጋፈጥ ፍላጎት ላላቸውም ለሌላቸውም ኃይሎች በመንግሥት ስም የገንዘብ ድጎማ ማድረግ፤
- ይህንን ውድድር አልባ የሆነ ምርጫም ለውጪ ዓለምና ለእርዳታ ሰጭ አገሮች እንደ ዲሞክራያዊ ተግባር ለማሳዬት ይረዳ ዘንድ የውጭ ታዛቢዎችን መጋበዝ፤
- ብዙ የተማረና ምናልባትም በሌላው ክልል አመለካከት ላይ “ተጽእኖ” ሊያመጡ ይችላሉ ተብለው የሚታመኑ ዋና ዋና ከተሞችን፤ በተለይም አዲስ አበባን ከሌላው ክልል ምርጫ ለይቶ ምንም ለውጥ በማያመጣ ጊዜ እነዲሆን ማድረግ፤
- በመጨረሻም እየተሰማ ያለው በዚህ በወያኔ ተውኔት ለመሳተፍም ተቃዋሚዎች የሥነ ምግባር ስምምነት ከወያኔ ጋር እንዲፈርሙ ማድረግ ነው።[3]

የ2002 ምርጫን በሚመለከት ወያኔ በሁለት ምዕራፎች ከፍሎ ያደረገው ዝግጅት ከላይ የዘረዘርናችውን ይመስላል። በሕዝብ ወገን ያሉ ተቃዋሚ ኃይሎች የዚህ የወያኔ ተንኮልና አፈና የመጀመሪያ ተጋፋጮች እንደመሆናቸው መጠን ይህንን ያጡታል የሚል ግምት የለንም። ከሕዝቡ አካባቢ የሚሰማው ስሜት ተቃዋሚዎች ምርጫ ውስጥ እንዲገቡ የማይፈልግ መሆኑን በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሕዝብ ለነኝሁ ተቃዋሚዎች እያሰማ መሆኑን ተቃዎሚዎች ከሕዝብ ጋር በሚያደርጉዋቸው ምክክሮች እያስታወቁ ነው፡፡ ግንቦት 7 ንቅናቄ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች እራሳቸው ካሉበት ዓይነተኛ ይዞታ በመነሳት ምርጫውን አስመልክቶ አስፈላጊውን ምላሽ እንደሚሰጡ ያምናል። ሆኖም ግን የዲሞክራሲና የአገር ማዳን ትግሉ አንድና በጋራም የሚመለከተን ጉዳይ ነውና እኛም ካለንበት ሁኔታ የሚታየንን ለአገር አቀፍ ትግላችን መደረግና መወሰድ ያለበትን አቋም የመግለጽ ግዴታ አለብን ብለን እናምናለን። በዚህም መንፈስ ግንቦት7 ምርጫ 2002ን አስመልክቶ የሚከተሉትን የትግል አቋሞችና ጥሪዎች ያደርጋል።

## 4. የግንቦት 7 ጥሪዎች

### 4.1. ጥሪ ኢትዮጵያ ህዝብ

ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመለስና የጥቂት ተባባሪዎችን መሠሪነት በምርጫም ሆነ በሌላ ሁኔታ መንገር “ቀባሪውን እንደ ማርዳት” ይቆጠራል። ሕዝባችን የሚፈልገው ከዚህ አፋኝና አገር አጥፊ የገዢ ቡድን እንዴት መላቀቅ እንደሚችል በተግባር ታግሎ የሚያታግለው ኃይል ነው። በዚህም መሠረት ግንቦት7 የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ 2002ን አስመልክቶ የሚያስተላልፈው መልዕክት የመለስ ቡድን በሰፊ የገንዘብ ወጭ፤ በማያቋርጥ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻና በመጠን የለሽ የሰው ኃይል ማሠማራት ለሚፈጥረው የማደናገሪያ ቲያትር ጆሮውን እንዳይሰጥ ነው።

---

[3] *ፊርማ ከወያኔ ጋር -- ፊርማ ከመለስ ጋር --ምን ማለት እንደሆነ የብርቱካን ሲቃይ ይንገረን ከማለት ሌላ ምን ማለት ይቻላል?*

ደግመን ደጋግመን ለሕዝባችን የምንለው ነፃ ምርጫ ምን እንደሚመስልና ምን ዓይነት ውጤት ማምጣት እንደሚቻል በ97 ምርጫ አሳይተሃል። በተጨማሪም የወያኔ ምርጫ  የራሱ የገዢው ፓርቲ ጨዋታ እንደሆነ በአለፈው የክልል ምርጫ በልዩ ልዩ መልኩ (ለምሳሌ ካርድን ከመቅደድ ጀምሮ እስከ ካርዱ ላይ ተቃውሞ እስከ መጻፍ ድረስ) እንዳደረኸው ለዓለም ሕዝብና ለራሱም ለወያኔ በማያሻማ መልኩ አሳይትሃል። ስለዚህም መጪውን የመለስን የምርጫ 2002 ጨዋታ ችላ ብለህ በሁሉ-ዓቀፍ ተሳትፎ ለዲሞክራሲና ለአገር ግንባታ የሽግግር ሥርዓት መምጣት አምርረህ ለመታገል ቆርጠህ ተነስ። ጉልበትህን፤ ንብረትህንና ቅዱስ የሆነውን መስዋዕትነትህን ለእውነተኛ ነፃነትና አንድነት ትግል ሳትቆጥብ አብረኸን እንድትሰለፍ ጥሪ እናደርጋለን።

### 4.2. ጥሪ ለሃቀኛ ተቃዋሚዎች

የመለስ-በረከት ቡድን በየደረጃው የተበተበውን የአፈናና የማደናገሪያ እርምጃ ገፈት ከእናንተ የበለጠ የቀመሰው የለም። በሕዝብ የተከበሩ መሪዎቻችሁ መታሠር ጀምሮ እስከ አባላቶቻችሁ በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መዋከብና መታፈን ምን እንደሚመስል ለእናንተ አይነገርም። እንድምታውቁት ከዚህ ሁሉ የእብሪትና የብልግና ድርጊቱ በኋላ ነውር የለሹ የወያኔ ቡድን ከእናንተ ትልቅ ችሮታ ለመጠይቅ ይመጣል። ይህም ችሮታ አሸናፊነቱን አስቀድሞ ባረጋገጠበት ሰአት የምርጫ 2002 አጃቢዎቹ እንድትሆኑ የተለመዱ አማላጆቹንና የማታለያ ቡርቲውን ይዞ ይቀርባል። በዚህም መለስ ከሠለጠነው ዓለም መድረክ ላይ በወጣ ቁጥር በግልፅም ሆነ በውስጠ ታዋቂ ቋንቋ የሚቀርብለትን የምርጫ 97 ዘራፊነቱን ክስ በእናንተ አጃቢነት ሊሰርዝ ይፈልጋል።

እናንት እኮ የነፃ ምርጫ ቅድመ ሁኔታዎችን የምታውቁ ብቻ ሳትሆኑ የእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ደራሲዎች ናችሁ። እናንተ እኮ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን አገዛዝ በተመለከተ "ብልጥ ልጅ የሰጡትን ይዞ ያለቅሳል" ከሚል የፖለቲካ ቀልድ እንዳለፈ የዓይን ምስክር ናችሁ።  ብዙዎቻችሁ እኮ በምርጫ 97 ሕዝባችን  ከድል አፋፍ በአጋዚ ጦር እየተደበደበ ወደ ታች እንዲወርድ ሲደረግ አብራችሁ ገፈቱን የቀመሳችሁ ናችሁ። ወያኔ ይህን ምርጫ ተብዬ እያዘጋጀ ያለው ዴሞክራሲያዊ ለመባል ብቻ ሳይሆን በእውነተኛ ምርጫ የደረሰበትን የ97 ውርደት እናንተን ምንም ልትንቀሳቀሱ በማትችሉበት ሁኔታ በውሸት ምርጫ አዋርዶ "በዝረራ አሸነፍኩ" ብሎ ለመፎለል ነው፡፡ እነሱ እንደሆን ለራሳቸው ምንም ክብር የላቸውም፡፡ ሕዝብ የሚያከብራቸውን ወገኖች እንደነሱ ሲዋረዱ ማየት ትልቅ ደስታ የሚሰጣቸው ህመምተኞች መሆናቸውን አትርሱ፡፡ ስለዚህ በእኛ እምነት አሁን የሚያስፈልገው ለሕዝባችን፤ ለዓለሙ ማኅበረሰብና ለራሱም ለወያኔ የመለስ-በረከት ቡድን፤ እነሱ የይስሙላ ምርጫ ሲሉና ሕዝቡና የሕዝብ ወገን የሆኑ ሁሉ ነፃ ምርጫ ሲሉ ያለውን ከፀሐይና ከጨለማ ያልተናነስ ልዩነት በድፍረት ማሳየት ነው። በዚህም እርምጃ እውነተኛ የሕዝብ ወገኖች ሳይጀመር ከወዲሁ በተጨናገፈ ምርጫ ገብቶ ከመተራመስ ይልቅ ለማይቀረው ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሕዝብን ማደራጀትና ማስተማር የበለጠ ጥቅም እንዳለው ግልጽ መሆን ይኖርበታል።

### 4.3. ለሚመለከታቸው የዓለም አቀፍ ኃይሎች ማሳወቅ ያለብን አቋም

በአገራችንና በአካባቢያችን ባሉ ጉዳዮች ላይ የፀጥታም ሆነ ሌላ ፍላጎት አለን የሚሉ ዲሞክራቲክ ሀገሮች በኢትዮጵያ ያለው የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ሥርዓት የመለስ አፈ ጮሌነትና ተራቀቅኩ ባይ የአንድ ሰው ቲአትር እንደሆነ ከተረዱ ሰንበተዋል። ከሰውዬው ቲያትር ሥር ያለው መንግሥት የጥቂት አምባገነኖች አገዛዝ እና በሙስና ከላይ እስከታች የተዘፈቀ መሆኑን ያውቃሉ፤ ሆኖም ግን የአገሪቱን የወታደራዊ፣ የፀጥታና የኢኮኖሚ ዋና ዋና  ክፍሎች በዘር ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው በሌሎች የዓለም ክፍሎች እንደታየው አደገኛ ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ ብለው ስለሚፈሩ ይጠነቀቃሉ። መለስና ቡድኑን የጂኖሳይድ ዋችና የሌሎችም የሰብዓዊ መብት ተሟጓቾች በየጊዜው የሚከሷቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህ መንግሥታት ይህንን በደንብ እንደሚያወቁት መረዳት አለብን።

ሆኖም ግን እነዚህ መንግሥታት በዲሞክራሲያዊ ዓላማ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ቢቆሙ እንኳን ሕዝብን ወይም የሕዝብ መሪዎችን ተክተው ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲና ደህንነት ይታገላሉ፤ ወይም ይህንን ሥርአት ያመጣሉ ማለት አይደለም። እንዳያውም የእለት-ተእለት የሀገራቸው ጥቅም ብዙ ጊዜ የቆሙለትን የዴሞክራሲ እምነት በሚጻረር መልኩ ከእንደ እነመለስና-በረከት ቡድን ዓይነቶች ጋር ሲያቆማቸው ደጋግመን አይተናል። ይህ ሁኔታ ምርጫ 2002ን አስመልክቶ አንዳንድ ግንዛቤን እንድንወስድ ያስገድደናል። የውጭ ኃይሎች ምርጫ 2002ን በሚመለከት እንደ ተለመደው "አንተም ተው አንተም ተው" አቀራረብ ተቃዋሚዎች ወያኔ ጋር እንድንሰለፍ ይጠይቃሉ። "ደግን ልጅ እናቱ አትወደውም" እንደሚባለውም "እሺ እሺ" የምንላቸውን ክፍሎች አጥብቀው ይጫናሉ።

አሁንም እንደተለመደው በሥልጣኑ የመጣን ሁሉ ወይ ፍንክች የሚለው ወያኔ እነዚህን የውጭ ኃይሎች እኔ በሚጠቅመኝ መንገድ ባዘጋጀሁት ምርጫ ተቃዋሚዎችን ካላመጣችሁ ማለቱ አይቀርም። ከዚህም አልፈው እነዚህ ኃይሎች ምርጫ በነፃነት እንዲካሄድ አጥብቀው እንገፋለን ካሉ የመልስ-በረከት ቡድን ከተወዳዳሪ ሌሎች አገሮች (ለምሳሌ ቻይና) ጋር የጠበቀ መቀራረብን እንደሚያደርግ ግልጽ ምልክቶችን እያሳዬ ነው። እንደሚታወቀው ይህንን ስናይ የመጀመሪያ ጊዜያችንም አይደለም።

እኛ ማድረግ ያለብን እኛ ለዲሞክራሲ፣ ለመልካም አስተዳደርና ኃላፊነት ላለው ሥርዓት ተገዢዎች እንደሆንን በአቋምና በተግባር አጥብቀን ማስረዳት ነው። ለዚህም ዋና መለያችን አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ተወዳድረን ለማሸነፍ የሚያስችለን ምንም ገደብ

የሌለብት ነፃ የምርጫ ሁኔታ ከመፍጠር በታች ምንም ድርድር ውስጥ እንደማንገባ በግልጽ ማቅረብ ይኖርብናል። እነዚህ የውጭ ሰዎች «ለምርጫው በቀረው አጭር ግዜ ውስጥ ለምታነሷቸው ትላልቅና ግዜ ወሳጅ እንዴት ምሳሽ መስጠት ይቻላል? የዛሬውን ግቡልና ለሚቀጥለው ምርጫ ነገሮች ይስተካከላሉ፤ ዴሞክራሲ ሂደት ነው» ማለታቸው አይቀርም፡፡ መልሳችን «ይህንንማ ከዛሬ አራት አመት በፊትም ሰምተዋል፡፡ ሁኔታዎች ሲብሱ እንጂ ሲሻሻሉ አላየንም፡፡ ዴሞክራሲ አዝጋሚ ሂደት የሚሆነው አብዛኛው ሕዝብና የፖለቲካ ልሂቅ ትርጉሙ ሳይገባው ሲቀር ነው፡፡ በአገራችን የዲሞክራሲ ትርጉም ፈጽሞ ያልገባቸውና ጣፋጭነቱ የሚመራቸው ዘረኛ በሆነ መንገድ ከገነቡት ሥልጣንና ጥቅም ይነቅናል የሚሉ ጥቂት ኋላቀር ዘረኞች ናቸው፡፡ ለጥቂት ዘረኞች ተብሎ ደግሞ የ80 ሚሊዮን ህዝብ የዴሞክራሱ ፍላጎት ሊገታ አይገባም» የሚል ሊሆን ይገባል፡፡ ግዜው አጭር ነው ለሚሉትም መልሳችን «ምርጫው ለሌላ ግዜ ይተላለፍ፡፡ በገዥው ፓርቲና በሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች መሃል እንዴት ምርጫውን ነጻና ፍትሃዊ ማድረግ እንደሚቻል በጋራ ጉባኤ ተቀምጠን መክረን ውሳኔ እስከምንሰጥ ምርጫው ይዘግይ» እንበላቸው፡፡

እኛ ለቆምንለት ሕዝባዊ ዓላማም ከሕዝባችን ጎን ቁመን በመሰለንና የተፈጥሮ መብታችንን ተጠቅመን በቆራጥነት እንደምንታገል ማሳዬት ይኖርብናል። ከዚህ በተረፈ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘላቂና እውነተኛ ወዳጅነት ከፈለጉ የአገሪቱን የፖለቲካ ችግር ሙሉ በሙሉ አፍኖ የያዘውን መንግሥት ሁኔታውን እንዲለውጥ የሚችሉትን ሁሉ እንዲያድርጉ መጠየቅና ከኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት፡ የአንድነትና የዲሞክራሲ ትግል ፊት በአደናቃፊንት እንዳይቆሙ አጥብቀን ማስረዳትና በማያወላወል መልኩ ማሳወቅ ይኖርብናል። በዚህ ጠንካራ አቋማችን ለጊዜው ተራው መልዕክተኛ ቢጮህም፤ ምናልባትም እነሱም ጊዜያዊ ፍላጎታቸውን ስላላሟላን ሊጋፉን ቢሞክሩም ውለው አድረው የሚያከብሩትና በሃገራችን ዕውነተኛ መፍትሄ ላይ በሚችሉትና በሚፈቅዱት ልክ እንዲያተኩሩ እናደርጋቸዋልን።

ለማጠቃላልም ሁላቸንም በሚቀጥለው ዓመት በመለስ-በረከት የተደገሰችልልን የማደናበርያ የመለስ-በረከት ምርጫ ዓላማዋ ምን እንደሆነ የተረዳን ይመስለናል፡፡ ለባርነት ቀንበር ህጋዊነት መስጠት ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ለዚህ «ኑና ላሞኛችሁ» የምርጫ ጥሪ መልሳችን የማያሻማ «አንዴ የተሞኘነው ይበቃል» ሊሆን ይገባዋል፡፡ መለስና-በረከት ለምርጫ ድግሳቸው ሲንደፋደፉ እኛ በእነሱ የድግስ ከበሮ ሳንደናገር ሁላችንም አቅማችን በሚፈቅድልን መጠን በሃገራችን ዴሞክራሲን እውን እንዲሆን ወደጀመርነው የምር ትግል ፊታችንን በጋራ እንድናዞር የግንቦት7 ንቅናቄ ይጠይቃል። የሀገራችን ሰው “ዱባና ቅል አበቃቀሉ እየቅል” እንዳለው ሁሉ እኛም ለወያኔ «የአንተ የማጭበርበሪያ ምርጫና ነጻ ምርጫ እየቅል» በማለት የሕዝብ ልጆች በአንድ ድምፅ እንንገረው!!

www.ginbot7.org/